# ጦቢያውያንና ጤንሳቸው

*በላይነህ አባተ* (abatebelai@yahoo.com)

ጤናን የአገራችን ሰዎች እንዴት እንደሚገነዘቡት ለመረዳት ከእለታት አንድ ቀን አዱን ጦቢያዊ ወይዘሮ ጤና ምንድነው? ምን ማለት ነው? ብዬ ጠየኩ። የምቀልድ መሰላቸውና "በወላላይቱ!! በጭንቅ አማላጅቱ! ተማሪው አንተ፣ የተማርከው አንተ! አንተ እወቀው እንጅ እኔን ትጠይቀኛለህ?" ብለው ሳቁብኝ። እኔ ግን መጠየቄን ቀጠልኩ። እውነቴን መሆኑ ሲገባቸው ቀኝ አገጫቸውንና ፊታቸውን በቀኝ እጃቸው አስደግፈው አንገታቸውን ወደ ቀኝ ዘንበል አድርገው የጌጣጌጥ ማስቀመጫ ሙዳያቸው የጠፋባቸውን ያህል ማዘን ጀመሩ። በልባቸው ያሉትን በትክክል የሚያውቁት እርሳቸውና አምላካቸው ናቸው። ለኔ የመሰለኝ ግን "ይህ ሰው እንኳን ሊማር ኮቢ አያያዝም እሚያውቅ አይመስል? ዝምብሎ መሸታ ቤት ሲያውደለድል የኖረ መሆን አለበት። እነ ሊቀ ሊቃውንት እገሌ፣ መምህር ምንትስ ባሉበት አገር እንዲህ አይነቱ ጅል ይፈጠር! ብላሽ! "ይብላኝ ለወለደሽ ያገባሽል ይፈታሻል አለ ተራች! ይብላኝ ለወለዱህ! እኔስ አለዛሬም አላገኝህ!" እያሉ ያዘኑብኝ፣ ያዘኑልኝም ይመስለኛል። በነገራችን ላይ በናንተና በኔ መካከል ይቅር እንጅ እኔን በራሴ ፈቃድ ከጃቸው ላይ ወድቄ የታዘቡኝን ያህል አብዛኛውን የዛሬ ዘመን ካባ-ደራቢና ቆብ-ደፊ የታዘቡ አይመስለኝም። (የኮሶ ሻጭዋን ልጅ ኮረጅክ አትበሉኝ። አልሸሹም ዘር አሉ ቢመስልም ያ ጎብዝ ያለው ራስ-ጠምጣሚና ዘንግ-ሰባቂ ይመስለኛል።) ወደ ጀመርነው ልመልስና ይንገሩኝ እጅ ብዬ ዳግም የጤናን ትርጉም እንደጠየኩ እንኳን በአገሪቱ ውስጥ እየሩሳሌም ያሉትንም የታወቁትን ታቦቶች በቅዱስ ጊዎርጊስ፣ በሃና ማርያም … እያሉ ከደረደሩ በኋላ "ድፍን ጦቢያ የሚያውቀውን ጉዳይ እንዴት ታጣዋለህ ልጄ! ጤና ጤንሳ ማለት ነዋ" ብለው በአንድ ቃል ተረጎሙልኝ። እኔም እኒህ የጦቢያ ወይዘሮ የቃል ትርጉም ባለማውቄ ይህንን ያህል ካፈሩብኝ አገር በሐራጅ የሚሸጡትን ቢያገኙማ እንኳን ያገራቸውን ታቦቶች የሰው አገር ቤተክርስቲያንም ስም ተበድረው ከመጥራት አልፈው ሰፌድ አንስተው ፊትን ደጋግመው የሚጠፈጥፉ ሳይሆኑ አይቀሩም በማለት ውስጥ ውስጡን እየሳኩና እየኮራሁባቸው ጤንሳ የምትለዋን ቃል ተቀብዬ ተለየኋቸው።

በኔ ግንዛቤ ጤንሳ የተለያዩ የጤንነትን ክፍሎች አካቶ የያዘ ባለ ብዙ ዘርፍ አብይ ቃል ነው። ጤንሳ ከበሽታ ወይም ከሚቆጠቁጥ ወይም ከሚያም ነገር ነጻ መሆንን ብቻ ሳይሆን የመንፈስን ፍትው ብሎ መጽዳትንም ያጠቃልላል። ጤንሳ በአካባቢው ካሉ ህይወት ካላቸውና ከሌላቸው ነገሮች ጋርም ተስማምቶ በጥሩ መንፈስ መኖርን ያካትታል። ወይዘሮዋ የአለም ጤና ድርጅት ዙሪያ ጥምጥም ሄዶ የተረጎመውን ጤና በአንድ ቃል ገልጠውታል። የአለም ጤና ድርጅት ጤናን እንዲህ ብሎ ያብራራዋል። "ጤና የበሽታ አለመኖር ብቻ ሳይሆን የአካል፣ የአእምሮና የማህብረሰባዊ ኑሮ ደህንነትም የሚያጠቃልል ነው። (1) (ትርጉም የራሴ)። ታልዳኑ ይሙት! እኔ የአለም ጤና ድርጅት ብሆን ኖሮ ቃላትንና ነጠላ ሰረዝን ስደረድር ከምውል የወይዘሮዋን ቃል እንዳለ እጠቀም ነበር። እርሳቸው እንደሁ "ፓተንት" የሚባል ነገር አያውቁ። በአፍሪካና በአንዳንድ የኤስያ አገሮች ዘቅጦ በሚገኘው የጤና ሁኔታ ሳቢያ የአለም ጤና ድርጅት የጤና ትርጓሜ ጥልቀት ብዙ ጊዜ ክርክር ያስነሳል። ሁኔታውን ይበለጥ ለማባባስ በአፍሪካ ሕዝቡን ሳይሆን ገዥዎችን ለማገልገል ክምር እንደሚንድ ዝንጀሮ ወንበር ላይ ጉብ ብለው የሚገኙት ሚኒስቴሮች የሕዝቡን ጤና በመበጥበጥ የአለም ጤና ድርጅት የጤና ግንዛቤ ትክክል አለመሆንኑ ለማረጋገጥ ተግተው የሚሰሩ ይመስላሉ። እንደ ጦቢያ ባሉ አገሮች ሕብረተሰቡ ጤና አድሮ የማያውቅ መሆኑን ለማረጋገጥ ምርምር ማድረግ የሚያስፈልግ አይመስለኝም። እንዲያውም ጤና አለማደር እንደ ልማድ ወይም ባህል የተቆጠረ ጉዳይ መሆኑን ወገኖቻችን ሰላምታ ሲለዋውጡ የሚባባሉትን ማስተዋል ይበቃል። አዎ ልብ ብሎ ላስተዋለው ጦቢያውያን ብዙ ጊዜ ሰላምታ ሲለዋወጡ ታሞ ያደረ ሰው የሚጠይቁ ነው የሚመስሉት። "በጎአችሁን አደራችሁ፣ ተሽሏችሁ አደረን? ወያ ቡልቲ? ጀጀባቴ ቡልቲ? ጤናችሁን ሰነበታችሁ?" ነው የሚባባሉት።

መድረስ የሚቻልበት እርከን ቢሆን በእውነቱ እኔም በበኩሌ ሙሉ ጤና ብዬ የምቀበለው ጦቢያዋ ወይዘሮ ወይም የአለም የጤና ድርጅት ጤና ብሎ የሚጠራውን ጤና ነበር። በሽታ፣ የአካል ወይም የአእምሮ ጉድለት ባይኖርብኝም፣ ሙሉ ጤነኛ ሰዎች ካሉበት የአለም ክፍል በመኖር ላይ ብሆንም፤ ወደዚች አለም አምጥቶ፣ አሳድጎ፣ ለቁም ነገር እንድበቃ ያደረገኝ ሕብረተሰብ ጤና አድሮ ስለማያውቅ እኔም ብዙውን ጊዜ ጤና አድሬ አላውቅም። ጤና ማህበረሰባዊ ጉዳዮችንም ያጠቃልላልና። መቼም የሰው ልጅ አስተሳሰብ የተለያዬ ነውና ያላየህ ያልሰማህ መስለህ፣ ያሳደገኝ፣ ያስተማርኝ ህብረተሰብ "ጅኒ ጃንካ" የሚለውን ድስኩርህን ትተህ ለምን ሙሉ ጤናህን አግኝተህ አትኖርም ብሎ የሚከራከር ሊኖር ይችላል። በእውነቱ ችግሩ እንደዚህ በቀላሉ እንጀራ ጎስጉዞ፣ ብርጭዎ ጨብጦ የሚፈታ ቢሆን እንዴት ደስ ባለኝ ነበር። እግዚአብሔርም እንበለው አንዱ ሐይል ፍጥረታትን በመልክ በመልኩ ፈጥሯል። (2) የሰውን ልጅም አንጎል የሚባል ነገር ካናቱ ላይ ሰርቶ ፈጠረው። አካባቢህን ቃኝ ተመራመር ብሎም ፈቀደለት። ተፈጥሮንና ፍጠረታትን ያጠኑ እንደ አርስቶትል ያሉ ሳይንቲስቶችና ፈላስፎችም ፍጥረታትን በመልክ በመልካቸው ፈርጀው ስም ሰጧቸው። ሰው አካባቢውን መቃኘት

የሚችል ከሌሎች ሁሉ የተለየ ፍጥረት ነው በማለት ደረጃውን ከፍ አድርገው ሰቀሉት።(3) እንግዲህ ይኸንን ሁሉ ዘንግቶ እየበሉ እየጠጡ፣ የበሉ የጠጡትንም ተጋድመው መልሰው እያገሱና እያጣጣሙ ብቻ መኖር ቀንበር ሲመልጣቸው ውለው ማታ ድርቆሽ ወይም ጭድ ጎርሰው እያመነዥኩ ሌሊቱን ከሚያነጉት ኩሊና ደመና ከሚባሉት በሬዎች ኑሮ ምን ልዩነት ይኖረዋል? "የሚጥምህን አንተ ታውቃለህ!" ብሏል ያ በግ ሻጭ። (የበግ ሻጩን ጉዳይ ለማንበብ ዋቢ-4ን ይጫኑ።) እንደኔ እንደኔ ራስ ቅል ውስጥ በተወሳሰበ መልክ የተሳሰሩ በትሪልዬን የሚቆጠሩ የነርቭ ሴሎች ተሸክሞ ጤናው የተሟላ እንሰሳ (sub-human) መስሎ ከመኖር ጤናው የጎደለ ሰው መሆን ይሻላል።

በዚህ ጥበብ ያለማቋረጥ በሚፈልቅበት ዛሬ ዘመን ሁሉ ነገር በሳይንሳዊ መንገድ በመለካት ላይ ይገኛል። በዚህም መሰረት የአንድን ሕብረተሰብ ጤንነት ሁኔታ የሚጠቁሙ አመልካቾች(indicators) አሉ። ጥቂቶቹ በሰንጠረዥ-፩ አንድ ላይ ሰፍረዋል። ከታች ይመልከቱ። ዳሩ ግን እንደ ጦቢያ ባሉ አገሮች ወግ ያለው መርጃ ወይም ስታስቲክስ የሚባል ነገር የለም። እንኳን የበሽታ አይነቶችና ምክንያቶች ሰው ሲወለድም ሆነ ሲሞት እንደማይመዘገብ የምናውቀው ጉዳይ ነው። እየለቃቀሙ ወረቀት ላይም ሆነ ዌብ ላይ ፈረንጆች የሚያስቀምጡት መረጃ በአብዛኛው የሚመነጨው ወንበርን ሲጢጢ...እያሰኙ እያስጮሁ በሱያቸው ሲያለፉ ከሚውሉ፣ የመርጃ ማዛባትን ቀጭን ትእዛዝ ከጎጆዎች ከሚቀበሉ፣ ራሳቸውን ጤና ጥበቃ ብለው ከሚጠሩ ጤና ብጥበጣ መስሪያ ቤቶች ነው። ከሕብረተሰቡ ሳይሆን የፌታቸውን መልክ ከሚያሳየው ጠረጴዛቸው ላይ የሚፈጥሩትን መረጃ የሚቀምሩትም በሕብረተሰቡ ጤና ላይ አዎንታዊ ለውጥ ያመጡ፣ የለውጥ ሐዋርያና ታታሪ ሰራተኛ እንዲያስመስላቸው አርገው ነው።

በቅርቡ አንድ በኤድስ ርዳታ ድርጅቶች ምርምራቸው የሚታገዝ መሆኑን የገለጡልን አንድ ፈረንጅ ከተወሰኑ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ "እየሁት" ያሉትን የጤና ሁኔታ ከአፍርካ እንደተመለሱ በአንድ የትምህርት ተቋም አዳራሽ ውስጥ በዘንጠረዥና በግራፍ መልክ አቀረቡ። በየሰንጠረዥና ግራፉ መካከልም ዝሆኖችን፣ አንበሳዎችን፣ አህዮችን፣ በኤድስ የሚሰቃዩ አፍሪካውያንን፣ በርሃብ እንክት ብለው የደረቁ ህጻናትን(ይህን ብዙዎች እንደ መዝሙር አዝማች የሚጠቀምበት ይመስለኛል) እየን። በጥያቄና አስተያየቱ ወቅት እኔም ተራ ደረሰኝና ጌታየ ሆይ ተዘዋውረውባቸው ያዩአቸው አገሮች አገዛዞች ምርምር እያደረገበት እንዳሉት ኤድስ በዋና የሰው ልጅ ሞት ምክንያትነት የሚመዘገቡ ናቸው። የጤና ጥበቃ ሚኒስትሮችም በነዚህ አገዛዞች ፈቃድ ተመስልጠው ወንበር ላይ ቁጭ የሚሉ ናቸው። ለመሆኑ እስካሁን የሰጡን የሰንጠረዥና የግራፍ የጤና መረጃ ከየት ነው ያገኙት? ምን ያህል እውነትነትስ አለው? ብየ ጥያቄን ሳልጨርስ የስብሰባው ተሳታፊ ሁሉ ፊቱን ወደኔ ዘወር አደርጎ እንደ ጉድ አስተዋለኝ። (የሰው ሁሉ አይን ፈጦ አየሁትና የጦቢያ አምላክ እርዳኝ አልኩ በልቤ) ተናጋሪው ግን አመልካች ጣታቸውን ወደኔ ቀስረው በይህ ሰው የሚያውቀው ነገር አለው ምልክ እያወዛወዙ ተክተክ ብለው ሳቁ። እኔም ሳዝን እንዳልቆየሁ ሁሉ መቼም ጥርስ ባዳ ነው አብሬ መሳቅ ጀመርኩ። ቀጥለውም ራሳቸውን አከክ አከክ አደረገና የዚህን መርጃ ትክክለኛነት (the validity of the data) መረጃውን የሰጡኝ የየአገሩ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች ቢ.መልሱት ይሻላል፤ እዳ ገባሁ(I am in trouble) ብለው አረፉ። ከዝግጅታቸው ይልቅ መልሳቸውን ወደድኩት። ለመሆኑ ሰውየው የጎበኟቸው የአፍሪካ አገሮች እነማን ነበሩ ብላችሁ አትጠይቁኝ። አጥብቆ ጠያቂ የናቱን ሞት ይረዳል ይባላልና። ለማንኛውም በሚኒስቲሮች ጽ/ቤት የተተጠነቀለውን ጥንቆላ እንኳን ብንቀበል በሰንጠረዥ-፩ ላይ እንደተመለከተው አማካይ ጤናማ እድሜአችን የሌሎችን ግማሽ ገደማ፣ የህጻኖቻችን አማሟት ከመቶ በላይ፣ የእናቶች አማሟት ደግሞ ከስምንት መቶ በላይ ከሌሎች የከፋ ሆኖ እናገኘዋለን።

ሰንጠረሽ-፩ ከዋና ዋና የጤንነት አመልካቾች ጥቂቶቹ

| አገር | አማካኝ ዘመነ-ህይወት | ጤናማ ዘመነ-ህይወት ** | ከ1000 ህጻንት ወስት የሚሞቱት ብዛት | ከ10, 000 እናቶች ውስጥ የሚሞቱት ብዛት | ከ100 ሰዎች የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ያላቸው | አስተያዬት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ስዊድን | 79 | 72 | 3 | 8 | ከተማ 100<br>ገጠር 100 | |
| ጃፓን | 79 | 72 | 3 | 10 | ከተማ 100<br>ገጠር 100 | |
| አሜሪካ | 75 | 67 | 7 | 14 | ከተማ 100<br>ገጠር 100 | ጥቁሮች ሳይጨመሩ ከስዊድን ይጠጋል |
| ኩባ | 75 | 67 | 5 | 33 | ከተማ 95 ገጠር 78 | |
| ኢትዮጵያ* | 50 | 41 | 109 | 850 | ከተማ 80 ገጠር 11 | አጠራጣሪ ቁጥሮች |
| ሴራሊዮን* | 37 | 27 | 165 | 2000 | ከተማ 75 ገጠር 45 | አጠራጣሪ ቁጥሮች |

Sources: Core Health Indicators: WHO http://www.who.int/whosis/database/core/core_select_process.cfm*እውነተኛ ስታትስቲክስ የሚባል ነገር የለም። ** ጤናማ ዘመነ-ህይወት ሰወች በጤንነት የሚያሳልፉት ዘመን ነው።

ሰው ሆነን የተፈጠርን ሁሉ በዚች አለም ላይ ስንኖር ይንስም ይብዛም፤ ለደቂቃም ሆነ ለዘመናት የሚያሳፍሩና አንገት የሚያስደፉ ነገሮች ይገጥሙናል። አንዳንዶቻችን በድምጻችን ስናፍር ሌሎቻችን በአከናፍራችን እናፍራለን። ከፊሎቻችን በተክለ ቁመናችን ስንሸማቀቅ አንዳንዶቻችን በችሎታ ማንስ እናፍራለን። ዝርዝሩ ብዙ ነው። እኔን በጦቢያ ልጅነቴ ከሁሉም በላይ ሁሌ አንገቴን የሚያስደፋኝና መሬት የሚያስጭረኝ ትልቁ መጽሐፍ በኤደን በመሰላት ምድር ተፈጥረን(2)፤ እንደ ጸደይ የጓሮ አበባዎች በሐምራዊ ቀለም አሸቆጥቁጦ አንድ ላይ አስቀምጦን፤ በጥፍ ድርብ ልሳን፣ ወግና ባህል አስውቦና አሳምሮ ፈጥሮን፤ የማይበርድ የማይሞቅ አየር ከምድር እስከሰማይ ዘርግቶልን፤ ተራራውን ከሜዳ፣ ቆላውን ከወይና-ደጋ ወይና-ደጋውንም ከደጋ አስማምቶ አንጥፎልን፤ ከፊሉን ቀዝቀዛ ሌላውን ሞቅ እያደረገ ሐይቁን፣ ወንዙንና ጅረቱን ከሰሜን እንስከደቡብ ከምስራቅ እስከምእራብ በመልክ በመልኩ አፍልቆልን እያለ ጦቢያውያን የሚበሉት፣ የሚለብሱትና የሚያድሩብት የሌላቸው፣ በሽታ ችጋርና መከራ በ41 አመት አማካኝ እድሜ የሚቀጥፏቸው፣ መዝገበ ቃላትና መጻሕፍት በርሃብና በርዛት በምሳሌነት የሚጠቅሷቸው ዜጎች ናቸው የሚባል ወሬ መስማት ነው። ይህ ጉዳይ በየአጋጣሚው አንገት ያላስደፋችሁ፣ እንቅልፍ ያልነሳችሁና ምን ይሻላል ያላሰኛችሁ ካላችሁ ያመለጣችሁበት መላ ለኔ ለወንድማችሁ አካፍሉኝ።

በአፍሪካና ምእራባውያን አገሮች መካከል ያለው የጤንነትም ሆነ የሌሎች ጉዳዮች ልዩነት አንድ ሁለት ተብሎ ተቆጥሮ የሚያልቅ አይደለም። የጤንነት ልዩነቱ በበሽታ በሚማቅቀው ወይም በሞት በሚረግፈው የሕዝብ መጠን ብቻ ሳይሆን በበሽታዎች አይነትና በሞት ዋና ዋና ምክንያቶችም ነው። ከታች ሰንጠረዥ-፪ሀና ለን ይመልከቱ ። በምእራቡ አለም ሕዝብ አብዛኛውን ጊዜ የሚሞተው ከሰው ልጅ አእምሮ በላይ በሆኑ ነገሮች ነው። በእርጅና፣ በካንሰርና ሌሎችም በአለም ላይ ካለው ቴክኖሎጅ ቁጥጥር ውጭ በሆኑ እንከኖች ነው። እንደ አለመታደል በአፍሪካ ሕዝብ እንደ ባህርዛፍ ቅጠል የሚረግፈው ግን የሰው ልጅ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በፊት አሳምሮ በተቆጣጠራቸው በተላላፊ በሽታዎችና በሌሎችም ባለንበት ዘመን ሰው ሊገሉ በማይገባቸው እንከኖች ነው። በአሁኑ ዘመን በምእራቡ አለም ምጥን ተከትለው በሚመጡ ምክንያት ወላድ ከሞተች እንደ ወንጀል ነው የሚታየው። በኛው ጉደኛ ያለም ክፍል ግን ገሻሮዎች የስዊዝ ባንክን ሰራተኞች በስራ ብዛት ሲወጥሩ ወላዶች በውላድ ምክንያት በየደቂቃው ያልቃሉ። ሕጻናት ኩፊን ባግባቡ በመያዝ ለማጥፋት በሚቻለው ወባ በየሰከንዱ እንደቅጠል ይረግፋሉ። ጉዳችን በዚህ አያልቅም። ከእነዚህ በሽታዎች ጋር ውድድር እንደገጠሙ ሁሉ መንግስት ነን የሚሉት አገዛዞችም ከወባ፣ ተስቦ፣ አንከሊስና ሳንባ ነቀሳ የተረፈውን በመግደል፣ በማሰር፣ በማስራብ፣ በማሰቃየትና በማሰደድ ወዘተ ይቀጩታል። አዎ በአፍሪካ እንደ ተቅማጥ፣ አንከሊስና ዘጊ-አናዳ ሁሉ "መንግስታት" በዋና የሞት ምክንያትነት (major causes of death) በሕዝብ የልብ መዝገብ ውስጥ ሲመዘገቡ ይውላሉ። ከታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

ሰንጠረዥ-፪ሀ የሞቱ ስዎች መዝገብ በአሜሪካ( ከእኛው ጋር ለማወዳደር እንዲረዳ)

| ሥም | እድሜ | የሞተበት ሰዓት | የሞተበት ዋና ምክንያት | ሌሎች ችግሮች |
|---|---|---|---|---|
| ጆን ስሚዝ | 95 | 1/23/2008 ከምሽቱ 10 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ላይ | የሳንባ ካንሰር | ሲጃራ |
| ሊዛ ካርተር | 102 | 9/24/2007 ከጥዋቱ ዘጠኝ ሰዓት ከ25 ደቂቃ ላይ | ድንገተኛ የልብ በሽታ | ሲጃራ |
| ሮበርት ዊሊያምስ ጁኒየር | 105 | 2/13/2006 ከምሽቱ ሰባት ሰዓት ከ12 ደቂቃ ላይ | ትንታ | የግብረ-ስጋ ግንኙነት ዝግመት |
| አሊሻ ሮናልድ ቡሽ | 112 | 4/3/2005 ቀን አስራ ሁለት ሰዐት ከሶስት ደቂቃ ላይ | ወድቀው | የቆዳ ድርቀት |
| ስቶን ፒተር ኢድዋርድስ | 89 | 11/5/04 ከጥዋቱ ሶስት ሰዓት ከሁለት ደቂቃ ላይ | የደም መርጋት | የማያንቀሳቅስ ውፍረት |
| አንድሪው ግሪን | 3 | 2/23/04 ከቀኑ ሁለት ሰዓት ላይ | መዋኛ ገንዳ ውስጥ ሰምጦ | - |

ሰንጠረዥ-፪ለ የሞቱ ሰዎች መዝገብ በጦቢ.ያ- የለም። ከእድር፣ ከእቁብ፣ ከቄሰ ገበዞችና ከሰፈር ሰዎች የሚገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት

| ሥም | እድሜ | የሞተበት ሰዓት | የሞተበት ዋና ምክንያት | የሕዝብ አስተያዬት |
|---|---|---|---|---|
| ሰውበሰው አዘነ | ገና ሮጦ ሳይደክም | የጥሊ.ያን ዱካ ሳይደርቅ | ለዙፋን ስላሰጋ ተሰቀለ | ወንድሞቹንም አጠፏቸው ይባላል |
| ዴማሙ ይመር | አመት ተኩል | የታህስስ ገብርኤል ዋዜማ | ተቅማጥና ትውከት | የሚላስ የሚቀመስም ከቤት አለነበረም |
| ኸድጃ ሁሴን | 19 ሳይሆናት አይቀርም | ኢ.ድ አልፈጥር ሁለት ቀን ሲቀረው | ምጥ ጠንቶባት | እናቷም እርሱዋን እንደወለደች ነው የሞተችው |
| እሸቱ ደበላ | 35 | የእንቁጣጣሽ ዋዜማ | ሳንባ ነቀርሳ | እህቱና ወንድሙም ታመዋል። መዳኒትም ጠፋ |
| ሙጩ አባቡ | 21 | የቁስቋም ለት | በአምስተኛ ረድፍነት ተጠርጦ ተረሸነ | ወንድሙንም እስር ቤት እንዳለ ደብድበው ገደሉት |
| ሐጎስ ኪሮስ | 42 | አቡነ-አረጋይ በዋለ በሳምንቱ | በእስር ቤት ሳለ በበሽታ ሞተ | ጓደኞችም በወንበዴነት ተጠርጥረው እስር ቤት ናቸው |
| ታንጉት አጥናፉ | 22 | የአስተርዮ ማርያም ለት | ንዳድ(ወባ) | ክሊኒክ ተመድረሷ በፊት ነፍሷ አለፈ |
| ዋቆ ረጋሳ | 18 | ግንቦት ውስጥ | በጥይት ሞተ | በተቃዋሚነት ተጠርጥሮ |
| እሸቱ ዘበርጋ | 35 | የመስቀል በነጋታው | መንገድ ዳር ወድቆ ተገኘ | ከነፍጠኞች ጋር ሲዶልት ተገኝቶ አሉ! |
| ከማል ቱፋ | 17 | በስኔ | በጥይት ተመቶ | አደገኛ ቦዘኔ ነው ብለው! |
| ዳንኤል ኢ.ራና | 21 | በስኔ | ከቤት አፍነው ወስደው በምን እንደገደሉት አይታወቅም | የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነበር |
| ግርማ አድማሱ | 20 | በታህሳስ | ዩኒቨርሲቲው በር ላይ ተኩሰውበት | ሰላማዊ ሰልፍ ሲወጡ |
| ጠልቶ ሜቶ | 5 | በሐምሌ | ትክትክ | ሁለት እህቶቹም በጠና ታመዋል |
| ያቆብ ደሌቦ | 25 | ግንቦት | ራሱን ገደለ | ከእንግሊዝ አገር ተመልስህ አገርህ ሂድ ቢሉት ከምመለስስ ብሎ ብሎ ራሱን አጠፋ |
| ቤተልሔም ደነቀው | 21 | አይታወቅም | ታንቃ ሞተች | አረብ አገር ተቀጥራ ትሰራ ነበር |
| ጅብሪል ከማል | 17 | አይታወቅም | በጦርነት | እናቱም ይህን እንደሰሙ በድንጋጤ አረፉ |

እርግጥ ነው እናትና አባትን በአገዛዝ ምክንያት ያጡ ልጆች “ወላጆቻችሁ እንዴት ሞቱ?” ተብለው ሲጠየቁ መንግስት ገደላቸው ብለው ሲመልሱ ይደመጣሉ። ልጆቻቸውን ወይም የትዳር ጓደኞቻቸውን በተመሳሳይ መንገድ የተነጠቁትም “መንግስት አይኔ እየየ ቀማኝ” እያሉ ሲያማርሩ ይሰማሉ። እንደኔ እንደኔ ዘመኑ በወለዳቸው የቴክኖሎጅ ውጤቶች ተወግደው ስማቸው እንኳን መረሳት ሲገባው ሕይወትን በለጋና በጎልማሳ እድሜ የሚቀጥፉት እንደ ወባ፣ ሳንባ ነቀርሳ፣ ተስቦ፣ ዘጊ-አናዳና ሌሎችም ሁሌ በገዳይነት መረገም የለባቸውም ነው። ተንፈላሰው እንዲኖሩ ሁሉን ነገር አመቻችተን ብንሰጣቸው እነሱ ምን ያድርጉ? እነዚህን በሽታዎችን ሙሉ ትጥቅ አስታጥቆ ሕዝብ እንዲፈጁ ያደረገ ሐይል ተቀምጦ ሰው በሞተ ቁጥር ወባ ቀጠፈው፣ ሳናብ ነቀርሳ ጠበሰው እያልን የእምዬን ወደ አብዬ አይነት ለቅሶ ማልቀስ ተገቢነት ያለው አይመስልም። አዎ በእነዚህ በሽታዎች ለሞቱ ዜጎች ሚሾ የሚያወርድ ሚሾኛ ሁሉ፣ ተስቦና ወባን እየወቀሰ ደረቱን ከመምታት ስንኙን፣ ግጥሙንና ቅኔውን ተንፈላሰው እንዲኖሩ ባደረጋቸው ሐይል ላይ መቀኘት ያለበት ይመስለኛል። ነጭ ለባሽ የህክምና ባለሙያም እንደዚሁ ወባ፣ ሳንባ ነቀርሳን፣ ተስቦና ሌሎችንም አለአበሳቸው በዋና የሞት ምክንያትነት ሲደረድር መዋሉን ትቶ የጠቅላላ ሞት ምክንያት “እርጉም-አገዛዝ” ብሎ ከሞቱ ሰዎች ስም ዝርዝር በቀኝ በኩል ከራስጌ በጉልህ ጾፎ የቀረውን በይወርዳል ምልክት (>>) ቢጨርስ ወደ እውነቱ ይጠጋል፤ ጊዜውንም ይቆጥብለታል በየ እገምታለሁ።

በአፍሪካ ምድር ገኘ·ዎች ሕዝብን የመግደል አባዜ እንደ ወባ አብሮ የሚኖር(endemic) በሽታ ነው። አንዳንዴ ቀጥተኛ የሆነ ገዥ-ወለድ የእልቂት ወረርሽኝ (epidemics) ሲነሳ ግን በሽታዎች ሁሉ ተዳምረው የማይስተካከሉት ይሆናል። የሩዋንዳን፣ የዩጋንዳን፣ የጦቢያንና በቅርቡ ደግሞ የኬንያን ጉዳይ ልብ ይሏል። (6-9) በቅርበት የምናውቀውን የራሳችንን ጓዳ

ብንመረምር አገዛዞች የግል አድርገው በሚያዝዛቸው ወታደሮችና ፖሊሶች በገጠር በከተማው በጭካኔ የሚያልቁት፣ በእየስርቤቱ የሚሞቱት፣ በዚህም ምክንያት በወላጅ ወይም ጧሪ እጦት የሚረግፉት ህጻናትና አሩግ፤ ሲሰደዱ በየውቂያኖስና በመርከብ ውስጥ እየታፈኑ የሚረግፉት፣ የዱር አውሬ የሚበላቸውን፤ በስደት አለም መንፈሳቸው ተናውጦ ራሳቸውን የሚገሉት ወዘተ ሁሉ ቢታሰቡ በእርጉም-አገዛዝ  አንቀልባ ታዝለው እሹሩሩ የሚባሉትን ተስቦ፣ ውባና ሳንባ ነቅርሳ ከሚፈጁትም ይበልጣል።

አሌክሳንደር ፍሌሚንግ (6) እ.ኤ.አ በ1928 ዓ.ም ፔኒሲሊንን ለአለም ካበረከተ ጀምሮ በሚያስደንቅ ፍጥነት ጸረ-ጀርም መድሃኒቶች በመፈጠራቸው፣ ቫክሲኖችን ጨምሮ የበሽታ መከላከያ መንገዶች ራእይ ባላቸው የሕዝብ መሪዎች ስራ ላይ በመዋላቸው በምእራቡ አለም ብዙዎቹ ተላላፊ በሽታዎች ጠፍተዋል። በአንጻሩ በእኛ አገር ርሃብንና እነዚህን በሽታዎች በመታገል ፋንታ አንዳንዴ ርሃብና ወረርሽኝ መኖሩን እየደበቅን፤ ሌላ ጊዜም መኖሩን እያመን "ሕዝብ እየረገፈነው ቶሎ እርዳታ ካልሰጣችሁ ዋ! እያልን" ልመና ሊሉት ማስጠንቀቂያ ግራ እሚያጋባ መላ እየፈጠርን፣ እርዳታውን ሞጭልፈን ለወንበር መጠበቂያ እያዋልን፤ ያለቀውን ሕዝብ ቁጥር አሐዝ ቢሮ ቁጭ ብለን እየቀነስን ሞት እሚባለው ሁሉን አስተካካይ ዳኛ በር አንኳኩቶ እኛ ጋ እስከሚደርስ እንኖራለን። እውነት ፍትህ ቢኖር በዚህ በያዝነው ክፍለ-ዘመን እንኳን በራሱ ገዥዎች ብትርና ባሩድ አሁን አገሪቱ ውስጥ ጎልተው በሚታዩት ተላላፊ በሽታዎችም ቢሆን የአንድም ጦቢያ ልጅ ህይወት መቀሰፍ አልነበረበትም። ከላይ እንደተገለጸው ተላላፊ በሽታዎች ሕዝብን እየቀሰፉ ያሉት በእርጉም-አገዛዝ የዉሃ አጠጭነትና ኮትኳችነት ነው። ባጠቃላይ ጦቢያውያን እንደ መብታቸው ሁሉ ጤንሳቸውም ከእግዚአብሔር እጅ ወጥቶ ያለው በሌላ "ሰው" እጅ ነው። እግዚአብሔር መብትና ጤንሳቸውን ወደነሱ እንዲመልስላቸው  ወይም እነሱን ወደ ወደ መብትና ጤንሳቸው እንዲያደርሳቸው የዘወትር ጸሎቴ ነው። አሜን።

*ዋቢ*


1. *Definition of Health; WHO http://www.who.int/about/en/ (accessed on 3/1/08)*
2. *ኦሪት ዘፍጥረት*
3. *Aristotle-Biology; The Internet Encyclopedia of philosophy http://www.iep.utm.edu/a/aris-bio.htm (accessed on 2/29/08)*
4. *የሚጥምህን አንተ ታውቃለህ http://addisvoice.com/article/Yemitim.pdf*
5. *Core Health Indicators: WHO http://www.who.int/whosis/database/core/core_select_process.cfm (accessed on 3/1/08)*
6. *Ruwandan Genocide; http://en.wikipedia.org/wiki/Rwandan_Genocide (accessed 3/08)*
7. *Id Amin Dada http://en.wikipedia.org/wiki/Idi_Amin*
8. *Civillian Protesters killed in Ethiopia; Washington Post http://www.washingtonpost.com/wp-dyn/content/article/2006/10/18/AR2006101800242.html (accessed on 10/06)*
9. *Kenya Turned in to killing field; BBC Africa; http://news.bbc.co.uk/2/hi/africa/7194744.stm (accessed on 3/08)*
10. *Alexander Fleming; http://www.time.com/time/time100/scientist/profile/fleming.html (accessed on 3/1/08)*


መጋቢት ሁለት ሺህ ዓ. ም.